በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Amhara National Regional State
Civil service commission

ቁጥር ሲሰኮ -7/17/621

ቀን፡27/01/2015 ዓ.ም

ለ---------------------------------------ቢሮ/ኤጀንሲ/ኢንስቲቲዩት/ባለስልጣን/ጽ/ቤት/መ/ቤት

**ባህርዳር፤**

ለ------------------------------------ዞን/ሬጅዮፖሊታን/ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ

-----------------

ጉዳዩ:- ስምሪት እንዲፈፀም የተፈቀደባቸው ተጨማሪ የስራ መደቦች ስለማሳወቅ ፤

በክልላችን የበጀት እጥረት ያጋጠመን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰው ኃይል ስምሪት እገዳው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽናችን በልዩ ሁኔታ ስምሪት መፈፀም የሚቻልባቸውን የስራ መደቦች በቁጥር ሲሰኮ.7/31/579 በቀን 20/12/2014 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ማስተላለፋችን ተከትሎ ከተለያዩ ተቋማት የሚነሱ ጥያቄዎችን መሰረት በማድርግ ተጨማሪ ማስተካከያ ማድረግ አስፈልጓል ፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ቁጥር በተፃፈ ደብዳቤ ያስተላለፍነው ሰርኩላር ደብዳቤ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

1. በታሳቢ የተቀጠሩ ወይም የተመደቡ ባለሙያዎች / ሰራተኞች እስከ ጥቅምት 30/2015 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታውን ያሟሉ ወይም የሚያሟሉ በጀት መኖሩ እየተረጋገጠ በምልመላና መረጣ መመሪያ መሰረት በደረጃ እድገት አግባብ በሚወጡ የውድድር ማስታወቂያዎች ተወዳድረው አሸናፊ መሆን እስከቻሉ ድረስ የስራ ደረጃውን ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ የተፈቀደ ሲሆን ስምሪቱ መፈፀም የሚቻለው እስከ ጥቅምት 30/2015 ዓ/ም ድረስ ብቻ የሚፈፀም ይሆናል ፡፡
2. ከሰኔ 30/2014 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 30/2015 ዓ/ም ድረስ በሰራተኛ ተይዘው የነበሩና በተለያዩ ምክንያት የሚለቀቁ ስራ መደቦች ላይ በጀት መኖሩን በማረጋገጥ በምልመላና መረጣ መመሪያ መሰረት እስከ ጥቅምት 30/2015 ዓ/ም ድረስ ብቻ ስምሪት መፈፀም እንዲቻል የተፈቀደ መሆኑን እናሳስባለን ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ካሣ አበባው ወንድማገኝ
ም/ኮሚሽነር

ግልባጭ:
- ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለም/ኮሚሽነ ጽ/ቤት

ሲ/ሰ/ኮሚሽን፣

☎ 0 58-220 -45-70 ☐20 28 fax 058-320-1698